- የሎጥ ሚስት ግን አልታዘዘችም።

ዘፍጥረት 19፡26

26- የሎጥ ሚስት ግን ወደ ኋላዋ ስለ ተመለከተች፣ የጨው ዐምድ ሆና ቀረች።

- እግዚአብሔር የሎጥን ሚስት የጨው ዐምድ አደረጋት።
- እግዚአብሔር የሎጥን ሚስት የጨው ዐምድ ያደረጋት ለምንድን ነው?

- የሎጥ ሚስት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጣስ ወደ ኋላዋ ስለተመለከተች ነው።

- የሎጥ ሚስት ወደ ኋላዋ የተመለከተችው ለምንድን ነው?

- ኃጢአቷን ትወድድ ስለነበር ነው።
- ኃጢአቷን መተው ስላልፈለገች ነው።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል።
- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁልጊዜ ይቀጣል።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ኃጢአትን በዘላለም ሞት ይቀጣል።

- እናንተም እንደ ሎጥ ሚስት ኃጢአታችሁን የምትወድዱ ከሆነ እግዚአብሔር በሞት ይቀጣችኋል።

- እናንተም እንደሎጥ ሚስት ኃጢአትን መተው የማትፈልጉ ከሆነ እግዚአብሔር በሞት ይቀጣችኋል።



## ትምህርት 21

1. በአብራምና በሎጥ መካከል የተፈጠረው ችግር ምን ነበር?
ሀ- አብራምና ሎጥ ብዙ በጎችና ከብቶች ስለነበሯቸው እንስሶቻቸውን የሚመግቡበት በቂ የግጦሽ ቦታ መታጣቱ ነበር።

2. ሎጥ በቆላማው ስፍራ ለመኖር የፈለገው ለምን ነበር?
ሀ- በዚያ በጎቹንና ከብቶቹን ለመመገብ በቂ የግጦሽ ቦታ ስለ ነበረ ነው።

3. ሎጥ የተሳሳተ ምርጫ ያደረገው እንዴት ነው?
ሀ- ሎጥ የተሳሳተው ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔርን ስላልጠየቀ ነው።
ለ- ሎጥ እግዚአብሔርን መስማት ስላልፈለገ ነው።

4. እኛ እግዚአብሔርን መስማት ካልፈለግን ምን ይደርስብናል?
ሀ- ወደ ዘላለሙ የእሳት ባሕር እንሄዳለን።

5. ብዙ በግና ከብት ወይም ሀብት ከዘላለሙ የእሳት ባሕር ያድነናል?
ሀ- አያድነንም።

6. እግዚአብሔር የሰዶምና የገሞራን ሕዝብ ክፋት አይቶ ነበር?
ሀ- አዎን።

7. የምናስበውን ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር መደበቅ እንችላለን?
ሀ- አንችልም።

8. የምንናገረውን ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር መደበቅ እንችላለን?
ሀ- አንችልም።

9. የምናደርገውን ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር መደበቅ እንችላለን?
ሀ- አንችልም።

10. ሎጥ ወደ ቆላማው ስፍራ ከሄደ በኋላ እግዚአብሔር ለአብራም ምን አለው?
ሀ- እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ሁሉ እንደሚሰጠው ነገረው።
ለ- ደግሞም እግዚአብሔር አብራም እንደ ከዋክብት የበዙ ዘሮች እንደሚኖሩት ነገረው።
ሐ- እግዚአብሔር የአብራም ዘሮች ወደ ሌላ አገር ሄደው እንደሚኖሩና ከ400 ዓመታት በኋላ ከዚያ መልሶ ወደ ከነዓን እንደሚያመጣቸው ተናገረ።

11. እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠው አዲስ ስም ማን ነበር?
ሀ- አብርሃም።

12. እግዚአብሔር ለሦራ የሰጣት አዲስ ስም ማን ነበረ?
ሀ- ሣራ።

13. እግዚአብሔር ለአብራምና ለሦራ አዲስ ስም የሰጣቸው ለምን ነበር?
ሀ- ብዙ ዘሮች ስለሚኖራቸው።

14. ሣራ መካንና ያረጀች ብትሆንም እንኳን፥ እግዚአብሔር ምን የሚል ቃል ገባላት?
ሀ- ሣራ የብዙዎች እናት እንደምትሆን።
ለ- ሣራ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ።

15. አብርሃምና ሣራ ዕድሜያቸው ስንት ነበር?
ሀ- የአብርሃም 100 የሣራ ደግሞ 90 ነበር።

16. እግዚአብሔር ሊያደርገው የማይችለው ነገር አለ?
ሀ- የለም።

- አብርሃምና ሎጥ ሁለቱም ብዙ በጐችና ከብቶች ስለ ነበሯቸውና ለከብቶቻቸው በቂ የግጦሽ ቦታ ስላልነበረ ተለያዩ።



- ሎጥ ኃጢአቱ የዘላለም ቅጣት እንደሚያስከትልበት ስላወቀ።

- ሎጥ እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል ስላወቀ።
- ሎጥ እግዚአብሔር እርሱን ለማዳን አዳኝ እንደሚልክ ስላመነ።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ በእርሱ የሚያምኑትን ያድናቸዋል።

- መላእክት ሎጥንና ቤተሰቡን ከከተማ ካስወጧቸው በኋላ ምን ተፈጸመ?

ዘፍጥረት 19፡24-25

24- ከዚያም እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያቃጥል ዲንና እሳት አዘነበባቸው።
25- እነዚያንም ከተሞችና ረባዳውን ምድር በሙሉ፣ በከተሞቹም የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ፣ የምድሩን ቡቃያ ሳይቀር ገለባበጠው።

- እግዚአብሔር የሰዶምንና የገሞራን ሰዎች ሙሉ በሙሉ አጠፋ።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ይጠላል።
- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ይቀጣል።
- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በዘላለም ሞት ይቀጣል።

- በኖኅ ዘመን እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ በጥፋት ውኃ አጠፋ።
- በሰዶምና በገሞራ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በእሳት አጠፋ።

- መላእክት ሎጥን ሚስቱንና ሁለቱን ሴቶች ልጆቹን ከሰዶም ሲያወጡ ሎጥና ቤተሰቡ ወደ ኋላ እንዳይመለከቱ ነገሯቸው።

14- ሎጥ ከቤቱ ወጥቶ የሴት ልጆቹ እጮኞች የሆኑትን አማቾቹን፣ «እግዚአብሔር ይህችን ከተማ ሊያጠፋት ነውና በፍጥነት ከዚህ ስፍራ ውጡ» አላቸው፤ አማቾቹ ግን የሚቀልድ መሰላቸው።

15- ሲነጋጋም፣ መላእክቱ ሎጥን «ከከተማዪቱ ጋር አብራችሁ እንዳትጠፉ ሚስትህንና ሁለቱን ሴት ልጆችህን ይዘህ ከዚህ ቦታ በፍጥነት ውጣ» ብለው አቻኰሉት።

16- ሎጥ ሲያመነታም፣ እግዚአብሔር ስለ ራራላቸው፣ ሰዎቹ የእርሱን፣ የሚስቱንና የሁለት ሴቶች ልጆቹን እጅ ይዘው ከከተማይቱ በደኅና አወጧቸው።

17- እንዳወጧቸውም፣ መልአኩ፣ «ሕይወታችሁን ለማትረፍ ፈጥናችሁ ሽሹ! መለስ ብላችሁ ወደ ኋላችሁ አትመልከቱ፤ ከረባዳው ስፍራ እንኳ ቆም አትበሉ! ወደ ተራራው ሽሹ፤ አለበለዚያ ትጠፋላችሁ» አላቸው።

- መላእክቱ የሎጥን የሚስቱንና የሁለት ሴት ልጆቹን እጆች ይዘው ከከተማይቱ አወጧቸው።

- እግዚአብሔር ሎጥን ያዳነው መልካም ሰው ስለ ነበረ ነው?
- አይደለም።

- እግዚአብሔር ሎጥን ያዳነው መልካም ሰው ስለ ነበረ አይደለም።

- ሎጥ እንደ ሰዶም ሰዎች ባይሆንም እንኳ ኃጢአተኛ ሆኖ ነው የተወለደው።

- ሎጥ እንደ ማንኛውም ሰው በኃጢአት ተወልዷል።

- ታዲያ እግዚአብሔር ሎጥን ለምን አዳነው?

- ሎጥ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ስላወቀ።



- አብርሃም ወዴት ሄደ?

- ወደ ኰረብታማ ቦታ (ወደ ደጋ)።

- ሎጥ ወዴት ነበር የሄደው?
- ወደ ረባዳማው ቦታ (ወደ ቆላ)።

- በቆላማው ቦታ የነበሩት ሁለት ከተሞች እነማን ነበሩ?
- ሰዶምና ገሞራ።

- የሰዶምና የገሞራ ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ነበሩ።
- በጣም ክፉዎች ነበሩ።

- እግዚአብሔር የሰዶምና የገሞራን ሰዎች ክፋት ያውቅ ነበር?
- አዎን።

- እግዚአብሔር ስለ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች ክፋት እንዴት አወቀ?

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያያል።
- እግዚአብሔር የማያየው አንድም ነገር የለም።

- እግዚአብሔር የሰዶምንና የገሞራን ሰዎች ክፋት ሁሉ አየ።

ዘፍጥረት 18፡20-21

20- ደግሞም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ «በሰዶምና በገሞራ ላይ የሚሰማው ጩኸት እጅግ በዝቶአል፤ ኃጢአታቸውም እጅግ ከፍቶአል፡

21- አድራጎታቸው እኔ ዘንድ እንደ ደረሰው ጩኸት መሆኑን ለማየት ወደዚያው እወርዳለሁ፤ እንደዚያ ካልሆነም፣ አውቃለሁ።»

- እግዚአብሔር ለረጅም ዘመናት ስለ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች ኃጢአት ያውቅ ነበር።

- የሰዶምና የገሞራ ሰዎች እግዚአብሔርን ረስተውታል እግዚአብሔር እነርሱን ረስቶአል?

- አልረሳም።

- የሰዶምና የገሞራ ሰዎች እግዚአብሔርን ረስተውታል እግዚአብሔር የእነርሱን ኃጢአት ረስቶአል?

- አልረሳም።

- ሰዎች እግዚአብሔርን ቢረሱት እርሱ ይረሳቸዋል?
- አይረሳቸውም።

- ሰዎች እግዚአብሔርን ቢረሱት እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይረሳል?
- አይረሳም።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን አይረሳም።
- እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአት በእርግጥ ይቀጣል።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአት የሚቀጣው ለምንድን ነው?
- እግዚአብሔር ፍጹም ስለ ሆነ።

- እግዚአብሔር ሰዎችን ፍጹም አድርጎ ስለ ፈጠረ።



- እኛስ እንደ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች ነን?
- አዎን።

- እኛ የሰዶምና የገሞራን ሰዎች የምንመስለው እንዴት ነው?
- እኛ ብዙ ውሸቶችን እንናገራለን።

- እኛም ሌሎችን በሐሰት እንከስሳለን።
- እኛም ጎረቤቶቻችንን እንረግማለን።

- እኛም የሌሎችን ንብረት እንሰርቃለን።
- እኛም ከሌሎች ሰዎች ሚስቶች ጋር እንተኛለን።

- እኛም ሌሎችን እንገድላለን።
- ከዚያ በኋላ መላእክቱ ምን አደረጉ?

ዘፍጥረት 19፡10-17

10- ከቤቱ ውስጥ የነበሩት እንግዶች ግን እጃቸውን በመዘርጋት ሰበው ወደ ውስጥ አስገቡት፤ በሩንም ዘጉ።

11- ከዚያም በሩን እንዳያገኙት በቤቱ ደጃፍ ላይ የተሰበሰቡትን ወጣቶችና ሽማግሌዎች ዓይን አሳወሩ።

12- ሁለቱ ሰዎችም ሎጥን እንዲህ አሉት፤ «በከተማዋ ውስጥ የሚኖሩ የአንተ የሆኑ ሰዎች አሉህ? አማቾች፣ ወንዶችና ሴቶች ወይም ሌሎች ዘመዶች ካሉህ ቶሎ ብለህ ከዚህ እንዲወጡ አድርግ፤

13- ይህን ስፍራ ልናጠፋው ነው። በሕዝቦቿ ላይ ወደ እግዚአብሔር የቀረበው ጩኸት ታላቅ በመሆኑ፣ እድናጠፋት እግዚአብሔር ልኮናል»

6- ሎጥም ሊያነጋግራቸው ወደ ውጭ ወጣ፤ መዝጊያውንም ከበስተኋላው ዘግቶ፣ እንዲህ አለ፤

7- «ወዳጆቼ ሆይ፤ እባካችሁ እንዲህ ያለውን ክፉ ነገር አታድርጉ።

8- እነሆ፣ ወንድ የማያውቁ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉኝ። እነርሱን ላውጣላችሁና የፈለጋችሁትን አድርጉባቸው። በእነዚህ ሰዎች ላይ ግን አንዳች ነገር አታደርጉባቸው፣ እኔን ብለው ወደ ቤቴ ገብተዋልና።»

9- እነርሱም «ዞር በል! ይህ ሰው ራሱ ትናንት ተሰዶ የመጣ ነው። ዛሬ ደግሞ ዳኛ ልሁን ይላል። ዋ! በእነርሱ ካሰብነው የከፋ እንዳናደርስብህ!» አሉት። ከዚያም ሎጥን እየገፈታተሩ የበሩን መዝጊያ ለመስበር ተንደረደሩ።

- የሰዶምና የገሞራ ሰዎች በጣም ክፉዎች ነበሩ።

- ሰዎቹ ብዙ ብዙ ውሸት ይናገሩ ነበር።
- ሰዎቹ በሐሰት ሌሎችን ሰዎች ይከስሱ ነበር።

- ሰዎቹ ጐረቤቶቻቸውን ይረገሙ ነበር።

- ሰዎቹ የሌሎችን ንብረት ይሰርቁ ነበር።
- ሰዎቹ ከሌሎች ሰዎች ሚስቶች ጋር ይተኙ ነበር።

- ሰዎቹ ሌሎችን ሰዎች ይገድሉ ነበር።

- ሌላው ቀርቶ ወንዶቹ ከወንዶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ይፈጽሙ ነበር።

- በዛሬው ጊዜ ያሉት ሰዎች እንደ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች ናቸው?
- አዎን።



- ሁሉም ኃጢአት እግዚአብሔርን መቃወም ስለ ሆነ።

- እግዚአብሔር የሰዶምና የገሞራን ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው ወዲያውኑ ያልቀጣቸው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር ከኃጢአታቸው ንስሐ እንዲገቡ ስለ ፈለገ።
- እግዚአብሔር ሊያድናቸው ስለ ፈለገ።

- በኖኅ ዘመን ሰዎች ከኃጢአታቸው ንስሐ እንዲገቡ እግዚአብሔር የጠበቃቸው ለምን ያህል ጊዜ ነበር?

- ለ120 ዓመታት።

- ሰዎች ንስሐ ባለመግባታቸው በመጨረሻው እግዚአብሔር ምን አደረገ?

- እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው የሚያጠፋ የጥፋት ውሃ ላከባቸው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ ይጠብቃል።
- ነገር ግን ሰዎች ንስሐ ካልገቡ እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል።

- እግዚአብሔር ዛሬ ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው ወዲያውኑ የማይቀጣቸው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ከኃጢአታቸው ንስሐ እንዲገቡ ስለሚፈልግ።
- እግዚአብሔር ሊያድናቸው ስለሚፈልግ።

- እግዚአብሔር ሰዎችን ማስፈራራት ብቻ እንጂ ስለ ኃጢአታቸው አይቀጣም?
- ይቀጣል።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ይቀጣል።

- እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን የሚቀጣበት ጊዜ ሲደርስ፥ እንዳይቀጣ ማድረግ የሚችል አለ?

- የለም።

- እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን የሚቀጣበት ጊዜ ሲደርስ ማንም ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ አይችልም።

- አንድ ቀን እግዚአብሔር ሁለት መላእክት ወደ ሰዶም ላከ።

ዘፍጥረት 19፡1-3

1- ሁለቱ መላእክት ምሽት ላይ ሰዶም ደረሱ፤ ሎጥም በሰዶም ከተማ መግቢያ በር ተቀምጦ ነበር። ሎጥም መላእክቱን ሲያይ ሊቀበላቸው ብድግ አለ፤ በግምባሩም ወደ ምድር ተደፍቶ እጅ ነሣቸው።

2- እርሱም፣ «ጌቶቼ፥ እባካችሁ ወደ እኔ ወደ ባሪያችሁ ቤት ጎራ በሉ፤ ከዚያም እግራችሁን ታጠቡ፤ አድራችሁም ጧት በማለዳ ጉዞአችሁን ትቀጥላላችሁ» አላቸው። እነርሱም፥ «አይሆንም፤ እዚሁ አደባባይ ላይ እናድራለን» አሉት።

3- ሎጥ ግን አጥብቆ ስለ ለመናቸው አብረውት ወደ ቤቱ ገቡ፤ ከዚያም ቂጣ ጋግሮ አቀረበላቸውና በሉ።

- እግዚአብሔር ሁለት መላእክቱን ወደ ሰዶም የላካቸው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር ሎጥንና ቤተሰቡን ሊያድን ስለ ፈለገ ነው።



- ከዚያ በፊት ሎጥ ይኖር የነበረው በሰዶም ከተማ አጠገብ ነበር።

- በዚያን ጊዜ ግን ሎጥ ይኖር የነበረው፥ በሰዶም ከተማ ውስጥ ነው።

- ከዚያ በፊት ሎጥ ክፋት በሞላበት በሰዶም ከተማ አጠገብ ይኖር ነበር።

- በዚያን ጊዜ ግን ሎጥ ይኖር የነበረው፥ ክፋት በሞላበት በሰዶም ከተማ ውስጥ ነው።

- ኃጢአት በሎጥ ሕይወት ውስጥ ምን እየሠራ እንደነበር አያችሁ?
- ኃጢአት ሎጥን ወደ ክፋት እየቀረበ እየቀረበ እንዲሄድ እየጐተተው ነበር።

- ኃጢአት በሁሉም ሰው ላይ የሚያደርገው እንዲህ ነው።
- ኃጢአት ሰዎችን ወደ ክፋቱ እየቀረቡ እየቀረቡ እንዲሄዱ ይጎትታል።

- ኃጢአት ሎጥን ወደ ሰዶም እንደሳበው ሁሉ ኃጢአት በሰዎች ሁሉ ላይ ምን ያደርጋል?

- ኃጢአት ሰዎችን ወደ ክፋቱ እየቀረቡ እየቀረቡ እንዲሄዱ ይስባል።

- መላእክት ሎጥን በጐበኙበት ጊዜ ምን ሆነ?

ዘፍጥረት 19፡4-9

4- ከመተኛታቸውም በፊት፣ የሰዶም ከተማ ነዋሪዎች የሆኑ ወንድ ወጣቶችና ሽማግሌዎች ከየአካባቢው መጥተው ቤቱን ከበቡት።

5- ሎጥንም ጠርተው፣ «በዚህች ምሽት ወደ ቤትህ የገቡት ሰዎች የት አሉ? ሩካቤ ሥጋ እንድንፈጽምባቸው ወደ ውጭ አውጣልን» አሉት።